## Editorial: Most Pleasing Posting From *Warka*: The Great Ethiopia

I have taken the liberty by posting what appeared in *Warka* (April 3, 2010) as one of the most profound statements I have read in years about the hope of Ethiopia's renaissance. By reposting such wonderful insights in my Website, I am imposing on my readers my deep commitment to bring back the glory of Ethiopia into the minced and fractured lives of Ethiopians despite the racist policies and activities of Arabs and the United States Government to divide and destroy Ethiopia. All Glory to Ethiopia and all of its diverse People. TH

ሰሞኑን በደቡብ ሱማሊያ በሰሜን ሱማሊያና በደቡብ ሱዳን የሰላም እና የእርቅ እንዲሁም የሬፈሬንደም ስብሰባዎች በመካሄድ ላይ እንዳሉ ይታወቃል ! በነዚህ ስብሰባዎች ተሳታፉ የሆኑት የሱማሌና የሱዳን ዜግነት ያላቸው ሰውች መካከል ኢትዮጵያዊ ነን የሚሉ ብዙ እንዳሉና ከዛም ባሻግር ከኢትዮጵያ ጋር መዋህድ እንፈልጋለን ! አንድ ነን ከኢትዮጵያ ጋር አንድ መሆን አለብን ! የሚሉት የስብሰባ ተሳታፊዎችም ሆነ መሪዎች መኖራቸው እየታወቀ ስለመጣ ቁጥራቸውም ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ መምጣቱ ስለታየ ኢትዮጵያ ወይንም ሞት የሚለውም አባባል በየስብሰባው እየተደመጠ መሆኑን ስለሰማን ከኢትዮጵያ እንዋሀዳለን ባዮችም ከእለት ወደ እለት ድምጻቸው ከፍ እያለ መምጣቱ አነጋጋሪ እየሆነ ስለመጣ ጉዳዩን በይበልጥ ለማረጋገጥና ለናንተ ለውድ ዋርካ አንባቢዎቻችን ለማሳወቅ ጋዜጠኞቻችንን ስበሳባዎቹ የሚካሄዱብት ቦታ ድረስ ልከን በቦታው ተገኝተው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር ቃለ መጠይቅ አድርገዋል ! እነሆ በዛሬ በአፕሪል አንድ ፕሮግራማችን "ኢትዮጵያ ልትሰፋ ነው " በተባለው ርእስ የጋዜጠኞቻችንን ቃለመጥይቅና ዘገባዎችን ይዘንላቹሁ ቀርበናል !!

ኢትዮጵያ ልትሰፋ ነው !

http://www.youtube.com/watch?v=sqBSD2GgBEQ
http://www.bergbook.com/images/22869-01.jpg
http://www.bergbook.com/images/22252-01.jpg
http://www.bergbook.com/images/18822-01.jpg

ወደ ዜይላ ከተማ የተግዋዘው ጋዜጠኛችን እዛ ከሚካሄደው የእርቅ ስብሰባ ውጪ ቆሞ ስብሰባውን ለመከፈት የተጋበዙትን የክብር እንግዳ - የቀድሞው የኢትዮጵያ መሪ መንግስቱ ሐይለማሪያምን ለማናገር ሞክሮ ነበር ! ግዋድ መንግስቱ ባሁኑ ሰዓት በሱማሌላንድም ሆነ በ ደቡብ ሱዳን የእርቅና ሰላም ስብሰባዎችን ለመምራት እየተመላለሱ መሆነቸውን ለመረዳት የቻለው ጋዜጠኛችን ለኮሎኔል መንግስቱ ስለሚመላለሱብት እኼህ አገሮች ከኢትዮጵያ ጋር የመዋህድ ስላላቸው ሀሳብና ፍላጎት ጋዜጠናችን ለጠየቃቸው ጥያቄዎች እንዲህ ብለው መልሰዋል !! ኢትዮጵያ ተበታትና ትጠፋልች ብለው የሚያሾፉትን በጭባጫዎች ስልጣን ቢኖረኝ ከፍተኛ እርምጃ እወስድባቸው ነበር ! የኛ መፈክር ኢትዮጵያ ትሰፋልች እንጂ ትጠፋልች አይደለም ! ስለመፈክር እኛን ጠይቁን ! ብለው ለቀረበላቸው ጥያቄ ባጭሩ መልሰዋል ! ተጨማሪ ጥያቄ ለማስተናደግ ፍቃደኛ ያልሆኑት ኮሎኔል መንግስቱ ..ለሌሎች ጥያቄዎቻቹህ ምውላ ከፈለጋቹህ በቅርብ ቀን የሚወጣውን መጽሀፌን ስትፈልጉ ገዝታችሁ አንብቡት ! ብለዋል - በተለመደው በቁጠኛው አንደበታቸው አቦ አትጭቅጭቁኝ ስሬዬን ልስራበት ብለው ግዋድ መንግስቱ ጋዜጠኛችንን ገፍትረው ወደ ስብሰባቸው ተመልሰው ስለገቡ ቃለመጠይቁ በዚህ መልኩ ተጠናቅዋል !!

http://www.somalilandtimes.net/images/78-c00.jpg

በደቡብ ሱዳን የተገኘው ጋዜጠኛችን ደሞ እዛ አካባቢ ከሚካሄደው የእርቅና የሰላም ስብሰባ ውጪ ቆሞ በዛ ስብሰባ እንደ አማካሪ ሆነው ጉባኤውን የሚመሩትን ሌላ የኢትዮጵያ ጦር ሰራዊት አባል ነበሩ ከሚባሉት ከጄኔራል ጻድቃን ለማነጋገር ችልዋል ! ጄኔራል ጻድቃን ስለ ደቡብ ሱዳን ከኢትዮጵያ ጋር መዋህድዋን ሲጠየቁ ምንጊዜም የማይለያቸው ግን ምንጊዜም የማይታየው አለቃቸው ሻቢያው ጃሜይካ እንደሌሉ ገልጸው የሰጡት መልስ ከአለቃቸው ጃማይካ ፍቃድ ውጪ መሆኑን አሳስበው በሚስጠርና በፍጥነት አንድ አንድ ጥያቄዎቻችንን ሲመለሱ እንዲህ ብልዋል -..አዎ ደቡብ ሱዳን ብዙ ኢትዮጵያዊ ነን የሚሉና ከኢትዮጵያ ጋር ውህደት የሚሹ ጠንካራ ቡድኖች አሉ ! ይሄ የደቡብ ሱዳን እና የኢትዮጵያ ውህደት ለአፍሪካ ቀንድም ሆነ

ለምስራቅ አፍሪካ ሰላም የሚያመጣን ለዛ ሰላም ዋስትና የሚሰጥ አንድ እና ብቸኛ አማራጭ መፍትሄ መሆኑን የሚገንዘቡ ብዙ አዋቂም ሆነ ተራ ግለሰብ እንዳሉ ሊያረጋግጡልን ችለዋል ! ሆኖም ግን የጋዜጠኞችንን ጥያቄ በጥያቄ የመለሱት ጄኔሬል ጻድቃን - ጥያቄው የውህደቱ መከናወን አስፈላጊነት ሳይሆን ደቡብ ሱዳን ከኢትዮጵያ ማለትም ጎንደርና ጋምቤላ ይሆን ? ወይንስ ከታላቅዋ ትግራይ / ትግሬኤርትራ ጋ ነው ይሁን ? ያ ነው ጥያቄው ብለዋል ! ስለነዚህ የጻድቃን ጥያቄዎች ማብራሪያ የጠየቀው ጋዜጠኞችን በቂ ምላሽ ሊያገኝ አልቻለም ! ጄኔራል ጻድቃን አርእስቱን ለውጠው እኔ እንደ ጃሜይካ አይደልሁም ..ኢትዮጵያ እንዳትሰፋ ከግብጽና ከአሜሪካኖች ከአረቦችም የምቀበለውን ገንዘብ ብቻዬን አልበላም ..ዘመዶቼም በቻጋር ሲያልቁ አላይም - የማገኛውን ገንዘብ ወደ አገሬ ነው የምልከው ብለው ከጋዜጠኞችን በመሸሽ ቃለመጠይቁን እንደ መንግስቱ ሀይለማሪያም በማስደንገጥ ሳይሆን በድንጋጤ ኢንተርቪውን አቅዋርጠው ጥለው ወደ ስብሰባቸው ሮጠው ገብተዋል !

http://www.cprdhorn.org/img/pic1edited.jpg
http://www.hebrezema.com/sitebuilder/images/tsadkan-164x194.jpg

ጅቡቲ ከሚገኘው ጋዜጠኞችን ጋር ለመነጋገር ፍቃደኛ የሆነው የጅቡቲ ፕሬዚዳንት ኡመር ጌሌ ስለኢትዮጵያ መስፋፋት እና ስለውህደት ደስትኛ ሆኖው ያለ ቁጣ ያለፍራቻ በአማሪኛ ቅዋንቅዋ ለጢያቂዎቻችን ፕሬዚዳንት ኦሜር ጌሌ ሰፊ መልስ ሊሰጡን ችለዋል ! ፕሬዚደንት ኡመር ጌሌ ቃለመጠይቁ በቢሮ ስራቸው እንዳይቅዋረጥ እና ብዙ ረብሻ እንዳይኖር ከፕሬዚዳንት ቢሮዋቸይ ይልቅ ሌላ ቦታ ይሻለናል በማለት ጋዜጠናችንን ሁምቡላ እና ቤንቤላ ሰፈር አጠገብ በሚገኘው የኢሀፓ ቢሮ ጋብዘውት ለጋዜጠናችን እንዲህ ብለው ነገረውታል - እኔ እኮ ስለጅቡቲና ኢትዮጵያ ውህደት አስፈላጊነት በይፋ በኢትዮጵያ ፓርላማ ተናግሬ ነበር ግን የሚያዳምጥ ጠፋ ! ነው ያሉት ! የጅብቲ ኢሳ ማለት የኢትዮጵያ ኢሳ ማለት ነው ያሉት ፕሬዚደት ጌሌ የኛ የምቡቲና የኢትዮጵያኖች ውህደት እና አንደንት የተራጋገጠው ዛሬ ሳይሆን በሚኒሊክ ዘመን ነበር በማልት ብዙ ታሪክ ጠቅሰው ለጋዜጠናችን አስተምረውታል ! ዛሬ ግን ..የሚያሳስበን በዛ ጊዜ የነበሩት ታላልቅ ጉዳዮች ሳይሆኑ የብርቱካን ነገር ነው ያሉት ፕሬዚደንት ጌሌ ጠረጴዛቸው ላይ ከተቀመጠው በኢትዮጵያ ፍራፍሬ ከተሞላው ቅርጫታቸው አንድ ብርቱካን አንስተው የብርቱካናችንን ነገር አደራ በማለት ጋዜጠኞችንን ብርቱካኑን ሰጥተው በክብር ሸኙተውታል !

http://www.addisfortune.com/Exports%20Leave%20Orange%20Market%20Undersupplied,%20High-priced.htm
http://www.johnennis.tv/wp-content/uploads/2009/07/HeartShapedOrange12.jpg

በደቡብ ሱማሊያ የሚገኘው ጋዜጠኞችን ደሞ እንዲሁ ተመሳሳይ መልካም መስተንግዶ የተሰጠው ሲሆን በሳቅና በፈግታ ጋዜጠኞችንን የተቀበለው የደቡብ ሱማሊያ የራህንወይን ህዝብ የእርቅና ሰላም ስብሰባ መሪ የሆነው ባለ ቀይ ሸሚዙ ሻቲግዱድ ኮሎኔል ሀሰን መሀመድ ኑር ነበሩ ! ሻቲጉዱድ ለጋዜጠናችን እንደገለጸው የደቡብ ሱማሊያና የኢትዮጵያ ውህደት ፕላን እና የፕላኑ ረቂቅ ለጊዜው በእጄ ባይኖርም ይህ ጉዳይ ተጠንቶ በብዙ ሱማሌዎች ከደቡብም ሆነ በስሜን /ሱማሌላንድ በዋርሴንጌሊም ሆነ በመሀል ሱማሊያ ሱማሌዎች ተቀባይነት ያገኘና የሚስማሙበት ነገር ነው ብለዋል ! ሙሉ ፕላኑን ለማወቅ ሁሴይን መሀመድን አነጋግሩ ብለው ጋዜጠኞችንን የጠቆሙት ኮሎኔል ሻቲጉዱድ ..በበኩሌ የራህዌይን ህዝብ ኢትዮጵያዊ ነው ብዬ ነው የማምነው ተመለስን አንድ የምንሆነበትን ቀን በጉጉት ነው የሚጠባበቀው ብለው ለጋዜጠኞችን አረጋግጠዋል !

http://www.globalresearch.ca/index.php?context=va&aid=4438

ውድ የዋርካ አንባቢዮቻችን ኮንጎ የሚገኙት ጋዜጠኞቻችን
በዚሁ ኢትዮጵያ ትሰፋለች በተባለው ርእስ ለመጪው ፕሮግራማችን
እየተዘጋጁ ስለሆኑ ስለኢትዮጵያ መስፋት እና ከኢትዮጵያ ጋር ውህደት ስለሚሹ
የአፍሪካ ህዝብና ሀገሮች ተጨማሪ ማስረጃና አስተያየቶችን ይዘንላቹህ እንቀርባለን !
በአሁኑ ሰዓት ከኮንጎ አገር ዌንዜ ኢትዮጵዮፒ ከተባለው ሰፈር - በሰፈሩ ውስጥ ከሚገኘው
ጋምቤላ ገበያ ከኮንጎሊዞች ጋር ቃለመጠይቅ እያደረግን ስለሆነ የኢትዮጵያ ትሰፋለች
ፕሮግራማችን ቀጣዩ ክፍልን እንድትከታትለኡ በመጋበዝ
በተመሳሳይ ፕሮግራም እስከምንገናኝ ድረስ

መልካም የአፕሪል ፉል ቀን እንመኝላቹሀለን !
ዓለማየሁ ነኝ ከጋምቤላ ገበያ ዌንዜ -ኢትዮፒ
http://www.youtube.com/watch?v=QGty5vh8y-U
http://www.youtube.com/watch?v=Xtz7de881qg

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኖራለች
http://www.youtube.com/watch?v=48c0Z02Je7Y

---
http://img28.imageshack.us/img28/3931/etho.jpg
http://img33.imageshack.us/img33/9715/alemayehu.jpg